# የሕዝባዊ ስብሰባ ጥሪ

እናት አገራችን ኢትዮጵያ እጅግ በጣም አሳሳቢና ወሳኝ በሆነ ታሪካዊ ወቅት ላይ ትገኛለች። *የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)፤* ባንድ በኩል የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት የሕዝባችንን የማይገሠስ መብት ዋነኛ መግለጫ የሆነውን በትረ-መንግሥት በነፍጥ ነጥቆ በሥልጣን ከተቆናጠጠ ጀምሮ የዴሞክራሲና ፍትህ ተሟጋቾችን እየጨፈጨፈ፤ በእስር ቤት እያጎረና አገራችንም ሰላም እንዳይኖራት በየማዕዘኑ ጠብ እየጫረ በማያባራ ጦርነት ውስጥ እየዘፈቃት በመሆኑ፤ በሌላ በኩል ደግሞ፤ *የ"ካልተባበራችሁ፤ ተሠባበሩ"* እርግማን ያለበት ይመስል በአንድ ግንባር መቆም ያዳገተው የተቃዋሚ ጎራ መኖር፤ እጅግ አሳሳቢና አነጋጋሪ ከሆኑት የወቅቱ ጉዳዮች ውስጥ ሁለቱና ዋነኞቹ ናቸው ብሎ ያምናል። በእነዚህና እነዚህን በመሣሰሉ ጉዳዮች ዙሪያ ከሕዝብ ጋር በግምባር ተገናኝቶ መወያየት እጅግ አስፈላጊና አንገብጋቢም ጉዳይ በመሆኑ የኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር በተለያዩ ሀገሮችና ከተሞች ውይይቶችን በማድረግ ላይ ይገኛል።

በካናዳም ለሚገኙ ወገኖቻችን የታቀደው የመጀመሪያ ስብሰባ በቶሮንቶ ከተማ እንዲደረግ ተወስኗል። ኢሕአፓን በመወከልም የድርጅቱ ከፍተኛ አመራር አባላት የሆኑት <u>ዶ/ር ጌታቸው በጋሻውና አቶ ታዬ ዘገየ</u> ስለአገራችን ህልውናና የወደፊት አቅጣጫ በጋራ ለመምከር የሚደረገውን ውይይት በግምባር ለመምራት በቦታው ስለሚገኙ፤ ጉዳዩ ለሚመለከታችሁ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ሁሉ የስብሰባው ተካፋይ እንድትሆኑ ጥሪያችንን በታላቅ አክብሮት እናስተላልፋለን።

- <u>ቦታው</u> ፦ 40 St. George street, Room # BA 1180, Bahan Centre Information T
  St. George and College St; (North West corner of St. George and College)
- <u>ቀኑ</u> ፡ እሁድ፤ April 1, 2007
- <u>ሰዓት</u> ፡ 2:00PM — 6:00PM

*የመሰብሰቢያውን አድራሻ ለማግኘት ችግር ከገጠመዎ፤ በ (647) 505-2226 ደውለው ያነጋግሩን።*

**በቶሮንቶና አካባቢው የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች**